መሰረት መጣል

በአለት ላይ የተመሰረተ

በእምነት ቃሉን በማወጅ የእግዚአብሔርን ኃይል ወደ አንድ ሁኔታ ውስጥ ከመልቀቅ የተሻለ ምንም ውጤታማ መንገድ እንደሌለ ከተሞክሮ ተምረናል።በእርግጥ፤ለበርካታ ጊዜ ለሰዎች ተናግሬያለሁ፤ነገር ግን አሁንም ከመናገር አልቦዘንኩም. . . ይህንን መንፈሳዊ የጦር መሳሪያን መጠቀም ባንችል ኖሮ ሩት ወይም እኔ በዚህ ቀን በሕይወት መኖራችንን እጠራጠራለሁ። ሁለታችንም በተለያዩ ጊዜያት በጠና ህመም ውስጥ አልፈናል፤እንደ እውነቱ ከሆነ፤በአንድ ነገር ተይዘን ነበር፤ወይንም አንድ ጫና የሚያደርግብን ነገር ነበር። ዳሩ ግን ዛሬ እዚህ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር፤ለቃሉ ኃይል እና ለሐኪሞች ምስጋና ይግባውና፤አሁንም በህይወት እና ጤነኛ ሆኜ ጌታን እያገለገልኩ እገኛለሁ።

ስለዚህ ዛሬ በዚህ ማለዳ ከኢሳይያስ ምዕራፍ 55፤10-11 ያለውን ምንባብ እናውጃለን፤ስለምንነጋገርበት ተከታታይ ጥናት የሚስማማ ነው፤

ዝናብና በረዶ ከሰማይ እንደሚወርድ÷ ምድርን እንደሚያረካት÷ ታበቅልና ታፈራም ዘንድ እንደሚያደርጋት÷
ዘርንም ለሚዘራ እንጀራንም ለሚበላ እንደሚሰጥ እንጂ ወደ ሰማይ እንደማይመለስ÷
ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፤ የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ
አይመለስም።

አሜን።

አሁን የዚህ የመጀመሪው የመልዕክት ርዕስ “በዓለት ላይ የተመሰረተ” የሚል ነው። ለዚህ ነው ይህንን በማጥናት የምንጀመርው። መጽሐፍ ቅዱስ ጥሩ የማስተማሪያ ሞዴል ነው፤እንዲሁም የተለያዩ የማስተማር መርሆችን ይከተላል። በተለይ አንዱ ከሚታወቀው በመጀመር ህዝቡን ወደማይታወቀው እንዲመራ ማድረግ ነው።ከማይታውቀው መቼም አትጀምርም፤በሚታወቅ ነገር ትጀምርና፤ከዚያ ተነስተህ ወደማይታወቀው ትቀጥላለህ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ከሚያደርግበት መንገዶች አንዱ፤በጣም ቀላል፤የተለመዱ፤የዕለት ተዕለት ልምምዶችን እና እንቅስቃሴዎችን መውሰድ እና መንፈሳዊ ትግበራዎችን መስጠት ነው። የተለያዩ ምሳሌዎች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አንድ ዘር ስለሚዘራ ገበሬ፤አንድ በመረብ ዓሣ ስለሚያጠምድ አሳ አጥማጅ፤እንዲሁም የጦር መሳሪያ ስለታጠቀ አንድ ወታደር ይናገራል። እንዲሁም ከዚያ ፍጹም በተለየ አውድ ደግሞ አንዲት እራሷን ለሠርጉዋ እያዘጋጀች ስላለች ሙሽራ ይናገራል። እነዚህ ስለዚህ ምርሆ ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው።

ነገር ግን ትኩረቴን ማድረግ የምፈልግበት ልዩ ሁኔታ አንድ ሕንፃን ስለ መገንባት ነው።እንደማስበውም ይህ የክርስትና ሕይወትን የሚያሳየው ስዕል በመጽሐፍ ቅዱስ ከሚገኙ ሌሎች ምስሎች ውስጥ በተደጋጋሚ ጊዜያት ተጠቅሞበታል።

ስለዚህ አስቀድመን ወደ ይሁዳ መልዕክት ቁጥር 20 እና 21 እንመለስ፤ይህ ለእኛ እንደ አማኞች ልባዊ ምክር ነው።

እናንተ ግን÷ ወዳጆች ሆይ÷ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ÷
ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ።

ስለዚህ በተቀደሰ እምነት እራሳችንን እናንጽ ዘንድ እንደሚገባን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።ይህ በህንጻ የተጠቀሰው ስዕላዊ መግለጫ የሚተገበርበት አንዱ መንገድ ነው።እራሳችንን እናንጽ ዘንድ ኃላፊነት አለብን።

በኤፌ 2፤21-22 በጌታ ዘንድ ስላለው ቅዱስ መቅደስ ይናገራል፡

በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤
በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።

ለእግዚአብሔር መኖሪያ እንሆን ዘንድ በመንፈስ አብረን ስለምንታነጽበት የጋራ የክርስቲያን ማህበረሰብ ይናገራል።።

እንዲሁም 1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 1፤4-5 ኢየሱስን እንደ ህያው ድንጋይ አድርጎ ይገልጸዋል፤ጴጥሮስ እንዲህ ይላል፤

በሰውም ወደ ተጣለ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ወደ ተመረጠና ክቡር ወደ ሆነው ወደ ሕያው ድንጋይ ወደ እርሱ እየቀረባችሁ÷
እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ÷ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ።

ስለዚህ በዚያ እያንዳንዳችን ጌታ የሚኖርበት መንፈሳዊ ቤት ለመሆን በአንድነት ከሚሰሩ ህያዋን ድንጋዮች ጋር ተነጻጽረናል።

እንዲሁም የመጨረሻው ምሳሌ፤ሐዋሪያት ስራ ምዕራፍ 20 ነው፤የጳውሎስ ስንብት እጅግ ልዩ በሆነ ፍቅር ለሚወዳቸው የኤፌሶን ሽማግሌዎች ነው፤ምክንያቱም የጳውሎስ አገልግሎት ምናልባት ከሌላ ስፍራ በበለጠ በኤፌሶን ትልቅ ተጽዕኖ ስለነበረው ይሆናል።በሐዋሪያት ስራ ምዕራፍ 20 ባለው ንግግሩ ስንብት እያደረገላቸው እና በህይወት መቼም እንደገና እንደማያዩት እየነገራቸው ነው። ለሁሉም በጣም አስደንጋጭ ሁኔታ ነበር። ይህ በእውነት በሐዋ 20፤32

ሊነግራቸው የፈለገው የመጨረሻው መልዕክት ነው።

አሁንም ለእግዚአብሔርና ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ።

አሁንም ለእግዚአብሔርና ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ።

ስለዚህ ጳውሎስ በእግዚአሔር የጸጋ ቃል እንታነጽ ዘንድ የሚረዳን ዋናው መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ይናገራል።እሱ ሊያንጸን እንደሚችል እና በእምነት ለኢየሱስ ክርስቶስ ለተለዩት በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን እንደሚሰጣቸው ይናገራል።

እንግዲህ፤እኔ የምገነባ አይደለሁም ነገር ግን አንድ ነገር አውቃለሁ። በማንኛውም ዘላቂ በሆነ ህንፃ፤ከጡብ ወይም ከድንጋይ ወይም ከሲሚንቶ ወይም አልፎ ተርፎም ከእንጨት ቢገነባ ወሳኙ ስፍራ መሰረቱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ሲሆን ለእያንዳንዳችን ትልቅ ጠቀሜታ ያለው ጉዳይ ነው። ትክክለኛ የሆነ መሰረት መመስረት ያስፈልጋል ምክንያቱም መሠረቱ የህንጻው ከፍታ፤ወርድ እና ክብደት የሚወስን ነው።መሰረቱ ገደቦችን ያስቀምጣል።ይህ በክርስትና ህይወት ውስጥ እውነት ነው። መሠረትዎ ከሚፈቅድልዎ የበለጠ ስኬታማ የክርስትና ሕይወት መገንባት አይችሉም። ይህ ዋናው ጉዳይ ነው፤የእርስዎ መሰረት ምንድን ነው? ትክክለኛውን መሰረት ጥለዋልን?

እንግዲህ አሁን፤በቂ እና ሙሉ የሆነ አንድ መሰረት ብቻ ነው፤እሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በ1ኛ ቆሮ 3 ላይ ሁለት ስዕላዊ መግለጫዎችን በመጠቀም ይጽፍላቸዋል። እሱ ግብርናን እንደ ስዕላዊ መግለጫ ይጠቀማል፤ነገር ግን ህንጻን ስዕላዊ መግለጫ በማድረግ ይቀጥላል። በቁጥር 9 ላይ እንዲህ ይላል፡

የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ፤ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ፤ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና።
የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ÷ ሌላውም በላዩ ያንጻል።
እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንጽ ይጠንቀቅ።
ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና÷ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ስለዚህ፤ጳውሎስ ለክርስቲያኖች ህይወት አንድ መሠረት ብቻ እንዳለና፤ያም ኢየሱስ ራሱ እንደሆነ ይናገራል።በዚህ መሠረት ላይ ያልተሰራ ማንኛውም ነገር የጊዜ እና ፍርድ ፈተና ላይ አይቆምም። ስለዚህ እያንዳንዳችን ህይወታችንን ምን ላይ እንደተገነባ መገምገም በጣም አስፈላጊ ነው። በእውነት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተመሰረትን ነን? እኛ በግል ህይወታችን ከኢየሱስ ጋር ለመገናኘት የሚያስችል የግል ሁበረት እና ስለ እሱ እውቀት አለን?

በኢየሱስ ላይ ይህን መሠረት የመጣል ጥያቄ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። እናም ይህን መሠረት እንዴት መመስረት እንዳለብን ያለውን ጉዳይ ለመመልከት ጊዜ ለመውሰድ እፈልጋለሁ፤ይህም በሕይወታችን ላይ የሚመሰረተው የኢየሱስ መሰረት ነው። ስለሆነም እያንዳንዳችሁ ህይወታችሁን፤መንፈሳዊ ሁኔታችሁን እና መንፈሳዊ ልምምዳችሁን እንድትመረምሩ እጋብዛችኋለሁ፤እንዲሁም ከመሠረቱ ጋር ያለዎት ግንኙነት ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ እፈልጋለሁ።

ወደ ማቴዎስ 16 መሰረታዊ አስተምርዎ መመለስ እፈልጋለሁ። በቁጥር 13 ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር እየተነጋገረ ነው፤እንዲህም አለ፤

> ኢየሱስም ወደ ፊልጶስ ቂሳርያ አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን፦ "ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ።እነርሱም፦ አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም ኤልያስ፥ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት።"

ከዚያም ጥያቄውን በጣም ግላዊ ሲያደርገው እንመለከታለን፤

> "እርሱም፦ እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው።
> ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፦ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ።"

ያ ለጴጥሮስ ህይወት እና ለመላው ክርስትና ታሪክ ወሳኝ አጋጣሚ ነበር።

> "ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፦ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ።
> ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ።
> እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።"

ስለዚህ ኢየሱስ ይህንን ከጴጥሮስ ጋር ያለውን ግንኙነት በኢየሱስ ክርስቶስ በራሱ ላይ እንድንመሰርት የሚያስችለንን መንገድ ለመመስረት ተጠቅሞበታል።

በመጀመሪያ በአጠቃላይ ጥቅም ላይ የዋሉ አንዳንድ ቃላት ላይ አስተያየት መስጠት አለብኝ። በቁጥር 18 ላይ

ኢየሱስ “አንተ ጴጥሮስ ነህ” አለው እና ግሪኩ ፔትሮስ ይለዋል፤ “እናም በዚህ ዓለት ላይ”፤ ግሪኩ ፔትራ ይለዋል፤ “ቤተክርስቲያኔን እገነባለሁ” ይላል። ብዙ ጊዜ ጴጥሮስ የቤተክርስቲያን መሠረት እንደሆነ ሲነገር ቆይቷል። እንደዛ ቢሆን ኖሮ መሰረት የሌለው የሚናወጥ ሕንፃ ይሆን ነበር እላለሁ—ምክንያቱም ከትንሽ ቆይታ በኋላ ኢየሱስ ገሠጸውና፤ “ወደ ኋላዬ ሂድ፤አንተ ሰይጣን” አለው። ከዚያም በኋላ ደግሞ፤ጌታን ሦስት ጊዜ ክዶታል። ከትንሣኤ በኋላ እንኳን፤ወንድሞቹ አይሁዶችን በመፍራት የወንጌል እውነትን ሲያመቻምች ጳውሎስ ይገስጸው ዘንድ ይገባ ነበር።ስለዚህ ቤተክርስቲያን በጴጥሮስ ሆነ በእኔ ላይ ባለመገንባቷ በጣም ደስተኛ ነኝ።

ከዚህ ምንባብ የምናገኘው፤የመጀመሪያው የግሪኩ እትም የሆነው የግሪኩ ኪዳን ውስጥ በጣም ግልጽ ሆኖ፤“አንተ ጴጥሮስ[ፔትሮስ]፤በዚህ አለት[ፔትራ] ላይ ቤተክርቲያኔን እገነባለሁ።” በማለት ተቀምጧል።

እንግዲህ በግሪክ ፔትሮስ ማለት ድንጋይ ወይም ትልቅ አለት ማለት ነው፤ከዚያ የገዘፈ ምንም አይነት አለት የለም።በመሰረቱ ሰዎች አንስተው አንድን ሰው ለመውገር የሚጠቀሙበት አይነት ድንጋይ ነው።በሌላ መንገድ ደግሞ፤ፔትራ ማለት ከዓለት ንጣፍ የተዘረጋ ስለታም አለት ማለት ነው።ብዙ ጊዜ ቀጥ ላለ የዓለት ገደል ጥቅም ላይ ይውላል፤ወይም በዚያ ባለ ደረጃ።ነገር ግን ልናስታውስ የሚገባን አስፈላጊው ነገር የዓለት ንጣፍ አንዱ አካል መሆኑ ነው።የአለት ንጣፍ ምንድ ነው? ጴጥሮስ ያለፈበት ነው፤ኢየሱስ ማን እንደሆነ የሚታወቀው መንፈስ ቅዱስ ሲገልጥ ብቻ ነው።

እናም ይህ ፔትራ ነው፤የክርስትና እምነታችን የተመሠረተበት መሠረት ነው። ግላዊ ህብረት እና የኢየሱስ የግል መገለጥ እንጂ እንደ አናጺው ልጅ፤እንዲሁም እንደ ታሪካዊ ሰው ሳይሆን እንደ ዘለአለማዊ፤ፍጡር ያልሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ነው።በዚያ ዓለት ላይ የምንገነባ ከሆነ፤ወደዚያ ነው ልንመጣ ይገባል። ጴጥሮስ ያለፈበትን ልምምድ ከእኛ ልምምድ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት።

እናም ብዙ ጊዜ ለሰዎች ተናግሬያለሁ፤አንድ ቤተ ክርስቲያን መግባት ትችላለችሁ፤ሐይማኖታዊ ክብረ በአል ልትፈጸሙ ትችላለህ፤ እንዲሁም ልትጸልዩ ትችላለህ፤ሆኖም ላትለወጡ ትችላለችሁ።ዳሩ ግን ኢየሱስን በእውነት ካገኛችሁ ትለወጣላችሁ። ከኢየሱስ ጋር ተገናኝቶ ያልተለወጠ ማንም ሰው የለም። ስለዚህ እያንዳንዳችን፤ “ህይወትን የሚቀይር የግል ህብረት ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ኖሮኝ ያውቃል?”ብለን መጠየቅ ያስፈልገናል።

በዚህ ግንኙነት ጴጥሮስ ያለፈበትን አራት ተከታታይ ደረጃዎች ልንጠቅስ እፈልጋለሁ። የመጀመሪያው፤መገናኘት ነው።ኢየሱስና ጴጥሮስ ፊት ለፊት ተገናኙ። በመካከላቸው ምንም መካከለኛ አልነበረም፤ካህን የለም፤በመካከላቸው ማንም አልነበርም።ቀጥተኛ እና ግላዊ የሆነ ግንኙነት ከኢየሱስ ጋር ነበር። እናም ወደ እዚህ ሁበረት ልንመጣ ይገባናል። ኢየሱስ በሌላ ስፍራ ላይ እንዲህ ይላል፤ "በሩ እኔ ነኝ። በእኔ በኩል ማንም ቢገባ ቢኖር እርሱ ይድናል።" "ወደ በእግዚአብሔር መንግሥት አንድ መንገድ ብቻ አለ፤ያም በበሩ በኩል ነው።በሩም ቤተ ክርስቲያን አይደለም፤የሐይማኖት አስተምርዎም አይደለም፤ኢየሱስ ብቻ እንጂ። "በሩ እኔ ነኝ።" ይላልና።

በሁለተኛ ደረጃ፤ግንኙነቱን ተከትሎ የሚመጣው ራዕይ ነው፤ራዕይ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በእግዚአብሔር አብ የተሰጠ ነው።ለዚህ ነው ኢየሱስ፤ "ሥጋና ደም ይህንን አልገለጠልህም።" ያለው። በተፈጥሯዊ መረዳትህ ወደዚያ ልትደርስ አትችልም፤ራዕይ ያስፈልጋል። አሁንም ይህ አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር በግል ካልገለጠ በስተቀር ማንም ኢየሱስን የእውነት ዘለዓለማዊ የእግዚአብሔር ልጅነትን ሊያውቅ አይችልም።ስነ መለኮትን ማጥናት ትችላላችሁ፤ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ መሄድ ትችላላችሁ፤ እንዲሁም አገልጋይ ልትሆኑ ትችላላችሁ። ነገር ግን፤እግዚአብሔር በግል ህይወታችሁ ክርስቶስን ካልገለጠላችሁ በስተቀር ኢየሱስን ማወቅ አትችሉም።ይህ መገለጥ የሚመጣው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር አብ ዘንድ ነው።

እስቲ ልጠይቃችሁ፤መልስ መመለስ አይጠበቅባችሁም፤ነገር ግን ከኢየሱስ ጋር ግላዊ ህበረት ኖሯችሁ ያውቃል? እኔ አለኝ። ከ50 ዓመታት በፊት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በአንድ የጦር ሠራዊት ሰፈር በሚገኝ ክፍል ውስጥ በነበረ ምሽት ነበር ኢየሱስን ያገኘሁት። እኔ ምንም ዓይነት መሠረታዊ የሐይማኖት ዕውቀት አልነበረኝም፤ ምንም የወንጌል ቋንቋ አልነበረኝም፤መዳኔን ወይም ዳግመኛ እንደተወለድኩ መናገር አልችልም ነበር፤ሁሉንም ነገር የተማርኩት በኋላ ነበር።ግን ልነግርዎ እፈልጋለሁ፤ተለውጬ ነበር—ፍጹም እና ዘላቂ በሆነ ሁኔታ ተቀየርኩ። በእርግጥ ፍጹም አልሆንኩም።እኔ አሁንም ፍፁም እንዳልሆንኩ ልነግርዎት እችላለሁ፤ ነገር ግን እኔ በተሻለ ሁኔታ ተለውጫለሁ።

እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ የሚገልጽልንን መቀበል አለብን። "አዎ፤እኔ አምናለሁ፤ተቀብያለሁ።" ማለት አለብን። አንድ ዓይነት ምላሽ መስጠት አለብን። ልማድ አይደለም፤ሆኖም በእኛ ውስጥ እየሆነ ያለ ነገር ይፈልጋል።

አራተኛ ደግሞ፤በኢየሱስ ላይ ያለንን እምነት በህዝብ ፊት መመስከር አለብን።ለዚህ ነው ኢየሱስ ጴጥሮስን "አንተ ክርስቶስ ነህ፤ መሲህ ነህ" ወደሚል ያመጣው።እሱ በሰዎች ፊት መሰከረ።ሰዎች ስለ እምነታቸውን በድብቅ ስለሚይዙ

ምስጢራዊ አማኞች ይናገራሉ፤በተለይም ራስዎን እንደ አማኝ ከተቀበሉ ሞት ሊያስከትሉ የሚችሉ አገራት ላይ ሚስጥራዊ አማኞች መኖራቸውን እቀበላለሁ።ነገር ግን ማንም ሰው የድብቅ አማኝ ሆነው በዘላቂነት ሊኖሩ ይችላል ብዬ አላምንም።

እስቲ ኢየሱስ በማቴ 10፤32-33 የተናገረውን ላንብብ፡L

"ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤
በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ።"

ስለዚህ ኢየሱስ በባህሪው መንገድ ሶስት ምርጫዎችን አይተዉም፤ሁለት ብቻ እንጂ። ትመሰክራለህ ወይም ደግሞ ትክዳለህ። በተገቢው ሁኔታ መመስከር ካልቻላችሁ እየካዳችሁ ነው።ስለዚህ እያንዳንዳችን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለንን እምነት በግልጽ የምንቀበልበት አንድ ነጥብ ላይ መምጣት አለብን።ይህ ለብዙዎች ወሳኝ አጋጣሚ ነው።

እኔ አማኝ ከሆንኩ በኋላ በሥራዊቱ ውስጥ ያገኘሁት ከሁሉ የተሻለው ነገር እነሱን ባገኘሁበት የመጀመሪያው አጋጣሚ ላይ ሁሉም ሰው እንዲያውቅ ማድረግ ነው። ከዚያም "ደህና፤በእርግጥ በመጀመሪያ ላይ አልነገርኳችሁም፤ ነገር ግን..." ብላችሁ ወደ ኋላ ልትመለሱ አይገባም። ስለዚህ አንድ ሃይማኖታዊ ልማድ ባልሆነ፤ነገር ግን በየምሽቱ በወታደር ክፍል ውስጥ አልጋዬ ጋር ወይም ሌላ ስፍራ ተንበርክኬ እጸልይ ነበር። ያም አብሯችሁ ላሉ ሰዎች የዚህ አይነት ሰው መሆናችሁን ይነግራቸዋል።ያን ማድረግ የበለጠ ቀላል ነበር። የተደበቁ ሌሎች ክርስትያኖችን አይቻለሁ፤ የሚያምኑትን በትክክል አይናገሩም ስለሆነም ከዚያ በኋላ ወደ ኋላ ተመልሰው ትክክለኛውን ምስክርነት መስጠት ይከብዳቸው ነበር። ስለዚህ፤ለእናንተ ያንን እንዳታደርጉ ሃሳብ አቀርባለሁ። በመንገድ ማዕዘን ላይ ቆማችሁ መስበክ አይኖርባችሁም ይሆናል፤ሰባኪ መሆን የለብዎትም። የቤት እመቤት መሆን ይችላሉ፤ ተማሪ መሆን ይችላሉ።የትም ብትሆኑ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመናችሁ ሰዎች ያውቁ ዘንድ ፍቀዱ፤እሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው።

ስለዚህ እነዚያን መሰረታዊ የሆኑትን አራት የመገናኘት ተከታታይ ደረጃዎችን ላጠቃልል፤ምክንያቱም ይህ እንዴት የክርስቶስን መሰረት በግል ህይወታችን እንደምንጥል የሚያሳይ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ፤ፊት ለፊት መገናኘት ነበር።

ሁለተኛ፤ በመንፈስ ቅዱስ በኩል በእግዚአብሔር አብ የተሰጠው ራዕይ ነበር።

ሦስተኛ፤ጴጥሮስ በመቀበል ምላሽ ሰጠ።

በአራተኛውም፤በህዝብ ፊት መስክርነትን ሰጠ።

እንግዲህ አሁን ሰዎች "እንደዚህ አይነት ራዕይ ዛሬ ሊኖር ይችላልን?" ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ። እንደ እኔ እና እንደ እናንተ ያሉ ሰዎች ልክ ጴጥሮስ እና ሌሎቹ ደቀመዛሙርት እንዳደረጉት ኢየሱስን በእውነት እና በግል ማወቅ ይቻላልን? ሁለት ወሳኝ ነገሮችን ማየት አለብን። በመጀመሪያ ደረጃ፤ኢየሱስ የአናጢው ልጅ ሆኖ ለጴጥሮስ አልተገለጠለትም። ለትንሽ ጊዜ በዚያ መንገድ ያውቀው ይሆናል። እሱ እንደ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ተገለጠለት። መጽሐፍ ቅዱስም በዕብራውያን ምዕራፍ 13፤8 ውስጥ እንዲህ ይላል፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።

በእርሱ ዘንድ ምንም ለውጥ የለም፤መቼም አይኖርም። እንግዲህ የቋንቋ ወይም የባህል ወይም የአለባበስ ጉዳይ አይደለም፤ነገር ግን ስለ ዘለአለማዊው የኢየሱስ ባህሪ ጥያቄ ነው። ለዚያም ነው ጴጥሮስ በሕይወቱ ውስጥ ምናልባት ለመጀመሪያ ጊዜ ኢየሱስን ያገኘው። ኢየሱስ ማን እንደሆነ መገለጥ ነበርው።

ሁለተኛ፤መገለጡ የተሰጠው ከመንፈስ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን ዘላለማዊ መንፈስ፤በጊዜ የማይገደብ ብሎ ይጠራዋል።ጊዜ፤ፋሽን፤ታሪክ፤ባህል፤ቋንቋ—መንፈስ ቅዱስን አይቀይሩም።

ስለዚህ በእነዚያ ሁለት ምክንያቶች እኔና እናንተ ጴጥሮስ ያገኘውን ይህን ቀጥተኛና የግል ራዕይ በእኩልነት እንዲኖረን ማድረግ ይቻላል። በመጀመሪያ ደረጃ፤እርሱ የተገለጠው ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ሁለተኛው ደግሞ፤የተገለጠው ዘለዓለማዊው መንፈስ ቅዱስ ነው።

አሁን ወደ ቀጣዩ ጠቃሚ ጉዳይ እንመጣለን፤መሠረቱን ከጣላችሁ፤እንዴት በእርሱ ላይ ትገነባላችሁ? በመጀመሪያ የተጠቀምንባቸውን ስለ ህንጻ የተነገሩትን ስዕላዊ መግለጫዎች ሁሉ ታስታውሳላችሁ። ስለዚህ በቀጣይ ወሳኝ እና ጠቃሚ የሆነውን ጉዳይ እንመልከት፤ በመሠረቱ ላይ እንዴት ትገነባላችሁ? በማቴዎስ ምዕራፍ 7 ላይ ኢየሱስ ወደ

ተናገረው ምሳሌ መሄድ እፈልጋለሁ፤ስለ ጠቢቡ ሰው እና ሞኙ ሰው የተነገረ በደንብ የታወቀ ምሳሌ ነው፤እያንዳንዳቸው ቤት ሠርተው ነበር ነገር ግን የሰሩት በተለያዩ መንገዶችን ነበር። ማቴ 7 ቁጥር 24 ጀምሮ፤

"ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት [ፕትራ]ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።
ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው÷ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም።
ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል።
ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው÷ ወደቀም÷ አወዳደቁም ታላቅ ሆነ።"

በመጀመሪያ ደረጃ፤እያንዳንዱ ቤት አንድ አይነት ፈተና የሚፈተን መሆኑን ማየት በጣም አስፈላጊ ነው። ከመፈተን ነጻ የሆነ ቤት አልነበረም። አንዱን ቤት የመታው ተመሳሳዩ ማዕበል ሌላውንም ይመታዋል። ስለዚህ የክርስትና ሕይወት ከማዕበል ነጻ የሆነ ህይወት አለመሆኑን ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። በማዕበል ውስጥ ታልፋላችሁ።እግዚአብሔር ፈተና አይደርስብህም ብሎ ማስተማመኛ መቼም ሰጥቶ አያውቅም።በእርግጥ፤ ጳውሎስና በርናባስ ለቀደመችው ቤተ ክርስቲያን "በብዙ መከራ ውስጥ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አለብን" በማለት ተናግረዋል።መከራ በሌለው መንገድ ላይ ከሆናችሁ፤ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚመራ መሆኑ አንደ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፤ምክንያቱም ጳውሎስ "በብዙ መከራ ውስጥ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አለብን" በማለት ይናገራል።በዚህ ንግግር ውስጥ ለምን በመከራ እናልፋለን የሚለውን የሚያስረዳ አይደልም ዳሩ ግን፤እመኑኝ፤እግዚአብሔር በመከራ ውስጥ ዓላማ አለው። እናም አሁን በመከራ ውስጥ ካላችሁ፤ተስፋ አትቁረጡ፤እሱ ያዘጋጀላችሁን እና በሌላ በማንኛውም መንገድ ልትማሩ ያልቻላችሁትን ፍጻሜ ታገኛላችሁ።

ያንን እንዴት እንደማውቅ ታውቃላችሁ? ከግል ተሞክሮ ነው። ብዙውን ጊዜ ንድፈ ሃሳቦች እሰብካለሁ። ስለዚህ ታዲያ ጥበበኛ ሰው እንዴት ይገነባል? በጣም ቀላል የሆኑ ሁለት መንገዶች አሉ። ኢየሱስ የተናገረውን እና የመጽሐፍ ቅዱስን ቃላቶች በመስማትና በመፈጸም ነው። ታዲያ ይህን መሠረት መገንባት የምትችለው እንዴት ነው? በተመሳሳይ መንገድ ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን በመስማትና ያንን ማድረግ ነው። አድማጭ ብቻ አትሁኑ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ለእነርሱ ምንም ተስፋ ቃል አይሰጥምና፤ ዳሩ ግን ሰምቶ ተግባራዊ ለሚያደርገው የተስፋ ቃል አለው።ምክንያቱም ተግባራዊ መሆን አለበትና። የቅዱሳን መጽሐፍትን እና የኢየሱስን ትምህርቶች በህይወት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።እንግዲህ በዚህ ስትጓዙ እግዚአብሔር እውነትን ለመተግበር የሚያስፈልጓቸውን አዳዲስ ቦታዎች በየጊዜው ይከፍትላችኋል።

እኔ ከሃምሳ ዓመት በላይ ክርስቲያን እንደሆንኩ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፤ነገር ግን እግዚአብሔር ቃላቱን ለመተግበር

አዳዲስ መንገዶች እያሳየኝ ነው።ተግባራዊ ላደርግ የሚያስፈልገኝ አዳዲስ የሕይወቴ ክፍሎች አሉ። የእኔ ሕንፃ አልተጠናቀቀም፤ በመገንባት ላይ ነው። እኔ ግን ብዙ ማዕበሎችን በተሳካ ሁኔታ ስላለፍኩ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ።

በሉቃስ ምዕራፍ 6 ውስጥ ተመሳሳይ የሆነ ኢየሱስ ሌላ ምሳሌ አለ፤እንዲሁም በጣም አስፈላጊ የሆነ ተጨማሪ አለ። ስለዚህ ወደ ሉቃስ ምዕራፍ 6 እዞራለሁ ከቁጥር 46 እስከ 49 ያለውን እንመልከት።እየተናገረ ያለው ኢየሱስ ነው።እንዲህ አለ፤

"ስለ ምን፦ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ ትሉኛላችሁ፥ የምለውንም አታደርጉም?"

በጣም አስፈላጊ ጥያቄ ነው።ታዛዥ ካልሆንክ ኢየሱስን ጌታ ብለህ መጥራት ከንቱ ነው ምክንያቱም "ጌታ" የሚለው የማዕረግ ስም አንድ ሰው ሊታዘዘው የተገባ ነው። በኑሮዎ ላይ ምንም አይነት ተጽዕኖ በማይፈጥር የቃላት ጋጋታ እንድንቆጠብ ኢየሱስ ይናግሯል።

እናም ይህንን ምሳሌ እንመልከት፡

"ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ ቃሌንም ሰምቶ የሚያደርገው፥ ማንን እንዲመስል አሳያችኋለሁ።
ቤት ሲሠራ አጥልቆ የቆፈረ በዓለት ላይም የመሠረተ ሰውን ይመስላል፤ ጐርፍም በመጣ ጊዜ ወንዙ ያን ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ ሊያናውጠው አልቻለም።
ሰምቶ የማያደርገው ግን ያለ መሠረት በምድር ላይ ቤቱን የሠራ ሰውን ይመስላል፤ ወንዙም ገፋው ወዲያውም ወደቀ የዚያ ቤት አወዳደቅም ታላቅ ሆነ።"

በማቴዎስ ውስጥ ያልተጠቀሰ አንድ አስፈላጊ ምንባብ በሉቃስ ውስጥ አለ። ስንቶቻችሁ እንዳስተዋላችሁት አላውቅም። አለቱ ላይ ለመድረስ የሚፈልግ ሰው በጥልቀት መቆፈር ነበረበት ይላል። በአለቱ ላይ ከመገንባቱ በፊት ብዙ ነገሮችን በማውጣት ማስወገድ ነበረበት።እናም ያ በብዙዎቻችን ዘንድ እውነት ነው፤ምናልባት ለሁላችንም ላይሆን ይችላል፤ነገር ግን በተለመደው የክርስትና ባሕል ውስጥ ያደግን አብዛኛዎቹ ልጆች ከአለቱ ዘንድ ከመድረሳችን በፊት ከመንገዱ ልናስወግድ የሚገቡ ብዙ ነገሮች አሉ። ሌሎቹ፤ደግሞ ሙሉ በሙሉ ከክርስትና ውጭ በሆነ ባህል ያደጉት ሌሎች ነገሮችን ማስወገድ አለባቸው፤ ዳሩ ግን እነሱ የተለዩ ይሆናሉ።

እንዲሁም ከመንገድ ላይ ቆፍረን ማስወገድ ያለብን አምስት ነገሮችን ልንጠቁም እፈልጋለሁ። የመጀመሪያዎቹ ወጎች ናቸው። አሁን ሁሉም ባህሎች መጥፎዎች አይደሉም፤እንዳንድ ትውፊቶች ጥሩ ናቸው። ሁሉንም ወጎች አውጥተን መጣል አያስፈልገንም፤ነገር ግን ኢየሱስ በዘመኑ ለነበሩ ሰዎች "በወጎቻችሁ የእግዚአሔር ቃል እንዳይሰራ

አደረጋችሁት” ብሎ ተናግሯል። በመጽሐፍ ቅዱስ መስመር ላይ ያልሆኑትን ወጎችን እያመናችሁ እና እየተገበራችሁ ነው።እናም እንደምልከታዬ፤አንድ ነገር መናገር አለብኝ፤ ኢየሱስ “በወጎቻችሁ የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሰራ አደረጋችሁት።” በማለት ለአይሁድ ሕዝብ የተናገረውን ተመሳሳይ ነገር ዛሬም በዚህ ዘመን ላለነውም ይናገር ነበር። ዳሩ ግን አይሁዶችን ብቻ አንመለከትም ምክንያቱም ይህ ብዙ የክርስትና የኋላ ታሪክ ላላቸው ሰዎች እውነት ነው—ከመጽሐፍ ቅዱስ መስመር ውጪ የሆኑ ባህሎችን፤የትግበራ መንገዶችን፤የምናደርጋቸውን ነገሮች፤የምንናገራቸው ቃላትን ሁሉ ወርሰናልና። ስለዚህ እርግጠኛ ለመሆን በጣም መጠንቀቅ ይኖርብናል።

ምንም ዓይነት የተወሰነ ሃሳቦችን ከማድረግ እቆጠባለሁ ነገር ግን ብዙ ልሰጥ የምችለው ነገር አለ። ልናስወግድ የሚያስፈልገንን ሁለተኛው ነገር ጥላቻ ነው። በአንድ ወቅት ላይ የተወሰነ ጥላቻ ያልነበረው ማንም ሰው የለም። ምናልባት እነሱን አስወግድሃቸው ሊሆን ይችላል። እኔ አላውቅም። ነገር ግን ሁሉም ዓይነት ጭፍን ጥላቻዎች አሉ።የዘር ጥላቻ አለ። እንደ አለመታደል ሆኖ፤ዓለም ዛሬ በዘር አድልዎ የተሞላ ነው። ለምሳሌ እንደ ደቡብ አፍሪካ ባሉ አገሮች ውስጥ እንደምናውቀው አስደናቂ ለውጥ ተገኝቷል።በተጨማሪም፤የዘር ጥላቻ የተወሰኑ ሰዎችን የቤተ ክርስቲያን አባል ከመሆን ያግዳቸዋል። ይህ ክፉ ሐሳብ ነው! ነገር ግን የዘር ልዩነት ጥላቻ የነገሰበት ስፍራ ይህ ብቻ አይደለም። የዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ በዘር ጭፍን ጥላቻ የተሞላች ናት እናም በብዙ ቦታዎች ዛሬም ይሸው ነው።

እኔ ከብሪታንያ የዘር ሃረግ የመጣሁት ነኝ፤እናም የብሪታንያ ህዝብ የራሳቸው የሆነ ጭፍን ጥላቻ አላቸው።ከብዙዎቹ ጋር አድጌአለሁ።እነሱን ለማስወገድ በጥልቅ መቆፈር ነበረብኝ። የራሴ የቤተሰብ መነሻ ከህንድ ነው። ሁሉም አያቶቼ በሕንድ ውስጥ ቡብሪታንያ ውትድርና ያገለግሉ ነበር። አሥራ ሁለት ዓመት ልጅ እያለሁ “ለምን አንድን ህንድ ለምሳ ስትጋብዙ አይቻችሁ አላውቅም” በማለት በየዋህነት መናገሬን አስታውሳለሁ።” እና በቤተሰቦቼ ውስጥ የተሰጠው ምላሽ በጣም አስደንጋጭ ነበር። ለዚህ ምክንያቱ ምንድ ነው? ብዬ አሰብኩ።በኋላ ላይ ግን ይህ ጭፍን ጥላቻ መሆኑን ተገነዘብኩ። እመኑኝ፤ ከተለያየ ዘር የመጡ በርካታ ሰዎችን እመለከታለሁ፤ ነገር ግን በጣም ጥቂቶች የሆኑት ከየትኛውም የዘር ልዩነት ጥላቻ ነፃ ናቸው።

እንዲሁም ሃይማኖታዊ ጥላቻ አለ። አብዛኞቻችን ለአንዳንዶቹ ሃይማኖታዊ አስተምርዎ በተቃራኒው አሉታዊ በሆነ መንገድ ምላሽ እንሰጣለን። አሁን ከጌታ ጋር ያለችው የመጀመሪያዋ ባለቤቴ፤ዬንማርካዊ ነበረች።እሷ ያደግችው

በዴንማርክ ሉተራን ቤተክርስትያን ውስጥ ነበር፤ከዚያም እነሱ በዴንማርክ ቋንቋ ጊንደርከር [ፎነቲክ]ብለው የሚጠሩትን የውሃ ጥምቀት፤የሁለተኛ ጊዜ ጥምቀት እንደ አማኝ በመውሰድ፤በአይናቸው ፊት አስደንጋጭ የሆነ ነገር አድርጋ ነበር። ምክንያቱም እሷ በዴንማርክ ትምህርት ቤት ስርዓት ውስጥ አስተማሪ ስለነበረች፤በመሰረቱ በአስተማሪነት መቀጠል ትችል ዘንድ በፓርላማ ፊት ቀርባ ነበር።ባለቤቴ እስከ መጨረሻ የህይወቷ ቀናት በሉተራን ቤተክርስቲያን ውስጥ ባለው የማያቋርጥ ጦርነት መቀጠሏን መናገር አለብኝ።ያንን አልደግፍም፤ያ በእሷ ዘንድ ድክመት ነበር።

ነገር ግን፤የአንድ የተወሰነ ቤተ እምነት አባል ስለሆኑ ሰዎች ስሰማ በግሌ የምማረው ነገር አለ፤እነሱን ሳላገኛቸው ስለ እነሱ በሚገባ የማውቅበትን አስተሳሰብ አዳብሬአለሁ። "ደህና፤እንደዚያ ሊሆኑ ነው፤እነሱ የተሳሳቱበት ስፍራ እዚህ ጋር ነው" እያልኩ አስባለሁ።የግል ተሞክሮዬ ብዙ አስተምሮኛል፤የሚቻል ከሆነ፤ ሰዎችን እስክታገኟቸው ድረስ አትፍረዱ።ምክንያቱም ከተሳሳተ የሃይማኖት አስተምርዎ የመጡ ነገር ግን ትክክለኛ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች አግኝቻለሁ።እንዲሁም በአንዳሩ ከትክክለኛ የሃይማኖት አስተምርዎ መጥተው የተሳሳቱ ሰዎች ደግሞ አሉ።ስለዚህ ለሐይማኖታዊ አስተምርዎ ጥላቻ መንገድ አትስጡ።

እንዲሁም ማህበራዊ ጭፍን ጥላቻ ደግሞ አለ። እንደገና፤ በማህበራዊ ጭፍን ጥላቻ የወጣ ሰው ምሳሌ ነኝ። ጭፍን ጥላቻ እንዳለብኝ እንኳን አላወቅሁም ነበር፤ነገር ግን በኤተን እና በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በብሪቴን እማር ነበር። እና የቀረው ዓለም እንዴት እየኖረ እንዳለ አላውቅም ነበር። ከዚያ ወደ የብሪታንያ ሠራዊት ውስጥ እንድገባ ተገደድኩ፤ከዛም አብሬአቸው ሆኜ ከማላውቃቸው ከተለያዩ ዓይነት ሰዎች ጋር ሆኜ እንድሰራ ሆንኩ። እናም ስለ እንግሊዝ ሕዝብ ምን ያህል እውቀቴ ውስን እንደነበር ተገነዘብኩ። በብሪታንያ ሠራዊት ውስጥ በቆየሁበት ለአምስት ዓመት ተኩል ስላገኙሁት ልምድ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ሆኖም ከበርካታ ማህበራዊ ጭፍን ጥላቻዎች ነጻ ሆኛለሁ።በዚያ በባለስልጣናት ቤተሰብ ሳለሁ እንደዚያ አስብ ነበር፤ዳሩ ግን ወደ ማህበረሰቡ በምወርድበት ጊዜ አንድ ትልቅ ነገር ተማርኩኝ። ከተመሳሳይ ደረጃ ላይ ሆናችሁ ሰዎችን ስትመለከቱ፤አንድ አቅጣጫ ላይ ያሉ ይመስላሉ።ነገር ግን ከታች ሆናችሁ ካያችሁ፤የተለያዩ ናቸው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ "እግዚአብሔር ሆይ፤ከታች ሆነው ለሚያዩኝ ሰዎች እንዴት ነው የምታያቸው?" ብዬ ሁልጊዜ አስባለሁ።

ስለዚህ፤የተለያዩ አይነት ጭፍን ጥላቻዎች አሉ። ግለሰባዊ ጭፍን ጥላቻ አለ። አንዳንድ ሰዎች በከፍተኛ ድምጽ የሚናገሩ ሰዎችን አይወዱም። አንዳንድ ሰዎች ቀይ ቀለም ጸጉር ያላቸውን ሰዎችን አይወዱም። ብዙዎቻችን ሁሉም ዓይነት የማይረቡ እና ግላዊ ጭፍን ጥላቻዎች አሉብን።እኔ ፖም ለሚያመነሻኩ ሰዎች ጥላቻ አለብኝ።በእውነት ከዚህ ለመውጣት እታገላለሁ፤ነገር ግን ያደገብኝ በመሆኑ አሁንም አብሮኝ አለ፤ምክንያቱም ያንን ድምጽ አልወደውምና።

ከዛ ባሻገር፤የተሳሳቱ አመለካከቶች አሉ፤ያም ስለ ኢየሱስ ማንነት ሙሉ በሙሉ ስህተት የሆኑ አመለካከቶች አሉ።ሙሉ፤ቅን እና ረጋ ያለው ኢየሱስ እንዲሁም በገና ግብዣ ላይ የሚገኘው፤ያ እውነተኛው ኢየሱስ አይደለም። እርሱ በጣም የተለየ ነበር፤ እጅግ በጣም አስደንጋጭ ጥላቻዎቻችንን እና የተሳሳቱ አመለካከቶቻችንን ለማስወገድ እሱ በጣም ዝግጁ ነው።

እንዲሁም የተሳሳቱ ግንዛቤዎች ሊኖሩን የሚችሉባቸው ሌሎች በርካታ መንገዶች አሉ። ክርስቲያን መሆን ምን ይመስል እንደሆነ ያሉ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች። ታዳጊ ሆኜ "ጥሩ ክርስቲያን ብሆን ኖሮ ቀሪው ሕይወቴ ሁሉ የተመሰቃቀለ ይሆን ነበር ።" ብዬ ለራሴ አስብ ነበር።እንደ ፓት ቦኒ እኔም፤ "ሰማይ የምድርን ሰባ አመታት መከራ ዋጋ አይኖረውም" ብዬ አስብ ነበር። ስለዚህ ኢየሱስን እስካገኝ ድረስ—ክርስቲያን የመሆን እድልን አስወገድኩ።

በጣም አደገኛ የሆነ ሌላ ነገር ደግሞ አለ፤ይህም አለማመን ነው። አንዳንድ ጊዜ ለማስተማር ስዘጋጅ፤አለማመንን ለማስወገድ ሁሉም ሰዎች አብረውኝ እንዲሆኑ በማድረግ እጀምራለሁ። ምክንያቱም አብዛኞቻችን በተለያዩ መስኮች ባለማመን ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን።በእውነቱ አዕምሮአችን ለእምነት ክፍት አይደሉምና።

በመጨረሻም፤ከሁሉም በላይ አስፈላጊው ነገር አመፅ ነው ብዬ አስባለሁ። ምናልባት "ይህና፤ወንድም ፕሪንስ፤እኔ ዓመፀኛ አይደለሁም።" ልትሉ ትችላላችሁ። ኦ፤አዎ ልክ ናችሁ አመጸኛ አይደላችሁም! ካላወቃችሁ ግን አንድ መሆናችሁ አይቀርም። አያችሁ፤እኔ ወደዚህ ሥነ-መለኮት መሄድ አልፈልግም፤ ነገር ግን የአዳም ዘር ሁሉ በዚህ ውስጣዊ አመጽ ተወልዷል።ይህን ዓመፀኝነት መለየት እና ማወቅ አለብን። እናም እግዚአብሔር ለአመጽ አንድ መድሃኒት ብቻ አዘጋጅቷል፤ያ ምን እንደ ሆነ ታውቃላችሁን? የሞት ቅጣት ነው፤ያ ትክክል ነው። እሱ ወደ ቤተክርስቲያን አይልከውም፤ወርቃማውን ህግ አያስተምረውም፤ እሱ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማስታወስ እንዲያውቅ አይረዳውም።ይልቁን ወደ ሞት ሰደደው እንጂ።ነገር ግን ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት የእግዚአብሔር ምህረት ተፈጸመ። አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር ተሰቅሏል።በውስጣችን ያለውን አመጽ ወደምንለይበት ስፍራ መምጣት አለብን፤ስለሆነም ያንን በፈቃደኝነት ለሞት እናቀርባለን።

አሁን ወደ መጽሐፍ ቅደስ መጥቻለሁ ምክንያቱም ይህ በክርስትና ሕይወት ውስጥ እንደ ማንኛውም ነገር አስፈላጊ ነው። ለመጽሐፍ ቅዱስ ያለዎት አመለካከት ምንድን ነው? ኢየሱስ ያለው ተመሳሳይ አመለካከት እርስዎስ አሎት? እኔ ከዮሐንስ ወንጌል አንድ ክፍል ላነብላችሁ እፈልጋለሁ፤ምዕራፍ 10፤35።እኔ ወደ ዓውደ-ጽሑፉ አልገባም ምክንያቱም ይህንን ለማድረግ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ኢየሱስ ግን እንዲህ አለ:

“መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው÷”

ያ በጣም ወሳኝ ጥቅስ ነው፤ምክንያቱም ኢየሱስ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ “የእግዚአብሔር ቃል” እና “ቅዱሳን መጻህፍት” በማለት ሁለት ዋና ዋና ስሞችን ይጠቀማል።እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔር ቃል ነው ብሎ ሲጠራው ከእግዚአብሔር የመጣ ማለት ነው፤ ከሰው የመጣ አይደለም። ምናልባት ከሰዎች ሰርጦች የመጣ ሊሆን ይችላል፤ነገር ግን ከእግዚአብሔር የመጣ ቃል ነው።

“መጽሐፍ ቅዱስ” የሚለው ሐረግ ገደብ ያለው ሐረግ ነው። ይህም በጽሑፍ የተቀመጠ ማለት ነው። እግዚአብሔር በጽሑፍ ያልተጠቀሱትን ብዙ ነገሮች ተናግሯል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በመለኮታዊ ስልጣን እግዚአብሔር የተናገራቸውን በጽሑፍ ይቀመጡ ዘንድ የወሰናቸውን ነገሮች ሁሉ ይዟል። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ነው።ያ ማለት የተጻፈ ማለት ነው።

ኢየሱስ ስለዚህ ጉዳይ አንድ ቀላል እና ጥልቀት ያለው መግለጫ ሰጥቷል። “መጽሐፍ ቅዱስ ሊሻር አይችልም።” ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የመጻፍ ምክንያትን ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ስልጣንን በተመለከተ የቻሉትን ያህል ሊከራከሩ ይችላሉ፤ነገር ግን ኢየሱስ ሁሉንም ነገር ተናግሯል።መጽሐፍ ቅዱስ ሊሻር አይችልም።ፍጹም ሥልጣን ያለው ነው። ሙሉ በሙሉ ይፈጸማል። በእሱ ውስጥ ያለው ሁሉም ነገር በትክክል ተፈጻሚ ይሆናል። የመቃወም አቋም ልትወስድ ትችላለህ፤ልትክደው ትችላለህ፤ነገር ግን ልትሽረው አትችልም።በእርግጥ፤ከካድከው፤በመጨረሻም ያጠፋዎታል።ቅዱሳት መጻሕፍት ሊሻሩ አይችሉም።

ሁላችሁም አንድ ጊዜ አንድ ላይ “ቅዱስ ቃሉ ሊሻር አይችልም።” እንድንል እጠይቃለሁ።

አሁን ዞራችሁ ከአጠገባችሁ ያለውን ሰው ተመልከቱ እና ዓይናቸውን እያያችሁ “ቅዱስ ቃሉ ሊሻር አይችልም።” ተባባሉ።

ደህና፤አሁን አንድ ነገር ተጠናቋል። አያችሁ፤ቅዱሳን መጻህፍትን መሳለቂያ ለማድረግ የሚደረጉ ከፍተኛ ትችቶች አሉ፤እናም በመጨረሻ ሙሉ በሙሉ ውጤታማ ያልሆነ መጽሐፍ ያደርገዋል። ዲያቢሎስ በህይወትዎ ውስጥ ሊያደርግ የሚፈልገው አንድ ነገር ካለ፤ ስለ እምነታችን የመጽሐፍ ቅዱስ ስልጣንና ትክክለኛነትን ዝቅ ማድረግ ነው።ዳሩ ግን እኛ እንደ ኢየሱስ ከሆንን በቀላሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ሊሻሩ አይችሉም እንላለን።ሰይጣን ሰምተኸኛል? ቅዱሳት መጻሕፍት ሊሻሩ አይችሉም። ደህና።

›

አሁን ቀጥዬ የምናገረው ነገር የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን፤ኢየሱስ ራሱ የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆኑ ነው። ይህ በዮሐንስ ወንጌል ሁለት ስፍራዎች ውስጥ ተጠቅሷል፤በዮሐንስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 1፤የታወቀ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው፤

በመጀመሪያው ቃል ነበረ÷ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ÷ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።

ያ የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው።እሱ ቃል ነበር፤እሱ ቃል ነው።
ዮሐ 1፡14 እንዲህ ይላል፤

“ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ÷ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን።”

ስለዚህ ኢየሱስ በተወለደበት ጊዜ፤የገና በዓል ብለን በማናከብርበት ወቅት ምንም እንኳ ጊዜው ባይሆንም፤ቃሉ ሥጋ ሆነ። ነገር ግን እርሱ ሁልጊዜም ቃል ነበር። እርሱ ዘለዓለማዊ የእግዚአብሔር ቃል ጋር ነበር።

እንግዲህ እርሱ ተመልሶ ሲመጣ፤እንዴት ተመልሶ እንደሚመጣ ታውቃላችሁ? ስሙ ማን እንደሚሆን ታውቃላችሁ? እስቲ ልንገራችሁ፤ ራዕይ 19ን እንመልከት። በመጀመሪያ እዚህ ሲመጣ እርሱ ቃል ስለሆነ፤ተመልሶ ሲመጣም እርሱ ቃል ይሆናል። ይህ እንግዲህ ኢየሱስ በክብር ከሰማይ ወደ በምድር መንግስቱን ለመመስረት ሲመጣ የሚያሳይ ስዕል ነው።የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 19፤11, 12 እና 13፤

“ሰማይም ተከፍቶ አየሁ÷ እነሆም አምባላይ ፈረስ÷ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል÷ በጽድቅም ይፈርዳል ይዋጋልም።
ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ናቸው÷ በራሱ ላይም ብዙ ዘውዶች አሉ÷ ከእርሱም በቀር አንድ እንኳ የማያውቀው የተጻፈ ስም አለው፤

በደምም የተረጨ ልብስ ተጐናጽፎአል÷ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል።"

ስለዚህ እሱ ሁልጊዜም ቃል ነው፤አሁንም ቃል ነው፤ቃልም ይሆናል።

ይህ ደግሞ በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገርን ያመጣል። በኢየሱስና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ሙሉ ስምምነት አለ። ለአንዱ ያለህ አመለካከት ለሌላው ያለህ አመለካከት ነው። ኢየሱስን አምነህ በአንጻሩ መጽሐፍ ቅዱስን አለማመን አትችልም።ያንን እውነታ ተቀብለሃል? ምክንያቱም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው። እርሱ ሥጋ የሆነ ቃል ነው።መጽሐፍ ቅዱስ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በጽሁፍ የተቀመጠ ቃል ነው። ለአንዱ ያለህ አመለካከት ለሌላው ከሚኖርህ አመለካከት ተመሳሳይ መሆን አለበት። በሁለቱ መካከል አጠቃላይ ስምምነት አለ።

እንግዲህ አሁን ሳጠቃልል በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ አምስት አስፈላጊ እውነታዎችን እና ከእሱ ጋር ያለዎትን ግንኙነት እንድንመለከት እፈልጋለሁ፤በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ውስጥ ተቀምጠዋል።ሦስት ጥቅሶች ናቸው፤ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የስንብት ንግግር እያደረገ ነው፤ እርሱ ሊሄድ እንደሆነ እያስጠነቀቃቸው ነው ስለሆነም ለጥቂት ጊዜ ለራቸው ይተዋሉ።ለደቀመዛሙርት እጅግ አሰቃቂ ጊዜ ነው፤ በዚህ መገለጥ በጣም እጅግ ተገርመው ነበር። ነገር ግን በዚህ መካከል ላይ ኢየሱስ እንደ አማኞች መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ የሚለንን አስደናቂ የሆነ መገለጥ ይሰጠል። በዮሐንስ ምዕራፍ 14:19 ውስጥ እንዲህ ይላል፡

"ገና ጥቂት ዘመን አለ ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም፤ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፤ እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ።"

ስለዚህ ኢየሱስ በዚያ በዓለም—ኢየሱስን በማያውቁት እና በእሱ ደቀመዛሙርት መካከል ልዩነትን አደረገ።ዓለም አያየኝም፤ነገር ግን ደቀመዛሙርቶች እኔን ያዩኛል አለ።

እንዲሁም ይሁዳ፤የአስቆሮቱ ይሁዳ ማለቴ አይደለም፤ነገር ግን ሌላኛው ይሁዳ በጣም ተገቢ የሆነ ጥያቄ ጠየቀ፤ቁጥር 22፡

"የአስቆሮቱ ያይደለ ይሁዳ ጌታ ሆይ÷ ለዓለም ሳይሆን ራስህን ለእኛ ልትገልጥ ያለህ እንዴት ነው?" አለው።

እሱ ይህንን የተናገረው ኢየሱስ ዓለም አያየኝም እናንተ ግን ታዩኛላችሁ ስላለ ነው።የሱ ጥያቄ የሆነው እራስህን ለዓለም ሳይሆን ለእኛ እንዴት ትገልጣለህ? የሚል ነው።አሁን ኢየሱስ የሰጠው መልስ አስፈላጊ በሆነ እውነት የተሞላ ነው።

> ‘‘ኢየሱስም መለሰ አለውም፦ የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን።’’

በኢየሱስ መልስ ውስጥ አምስት ወሳኝ እውነታዎችን መውሰድ እፈልጋለሁ።በመጀመሪያ፤ኢየሱስ ለዓለም ሳይሆን ለደቀ መዛሙርቱ እራሱን እንደሚገልጥ ተናግሯል።ደቀ መዛሙርቱንና ዓለምን የሚለይበት ልዩ ምልክት ምንድን ነው? መልሱ የእግዚአብሔርን ቃል መጠበቅ ነው። እውነተኛ ደቀ መዛሙርት የኢየሱስን ቃሎች ይጠብቃሉ። ስለሆነም በሃይማኖታዊ ስያሜዎች የተመረጡ አይደሉም፤ይልቁን ከቃሉ ጋር በተዛመዱበት መንገድ የተመረጡ ናቸው። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያላችሁ ግንኙነት እውነተኛ ደቀመዝሙርት እንድትሆኑ የሚያደርጋችሁ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል መጠበቅ ደቀ መዝሙሮችን ከዓለም የሚለይ ነው።

ስለዚህ በዚህ ማለዳ በዚህ ጉባዬ ውስጥ የመንገኝ እያንዳንዳችን ከእነዚህ ሁለት መደቦች ውስጥ አንዱ ነን። ደቀ መዛሙርት ከሆንን የእግዚአብሔርን ቃል እንጠብቃለን።የእግዚአብሔርን ቃል የማንጠብቅ ከሆነ ከዓለም እንሆናለን—ከዓለም የሆነ ደግሞ ከኢየሱስ ጌትነት ስር አይደለም።

ሁለተኛው እውነት ደግሞ ኢየሱስ፤ “ማንም የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል።” በማለት ይናገራል። ስለዚህ፤ የእግዚአብሔርን ቃል መጠበቅ ማለት ደቀመዝሙር ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር የሚፈተንበት ትልቁ ፈተና ነው።እንደ አማኞች ፍርአት ምክንያት አለመሆኑን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው፤ምክንያታችን ፍቅር ነው።በአንድ በኩል፤ሕጉ የፍርሃት ምክንያትን ተጠቅሟል። ይህን ካደረጋችሁ ትቀጣላችሁ። ሆኖም አሁን የሚሰራ አይደለም። እኔ ብዛት ያላቸውን ልጆች ለማሳደግ አገዛ አድርጌአለሁ። አንዳንዶቻችሁ ምን ያህል እንደሆኑ አታውቁም፤ወደ እዚያ ያህል አልገባም። ነገር ግን እንደ ወላጅ በእናንተ ቁጥጥር ስር በሆኑበት ጊዜ ልጆችን በማስፈራራት ልትቆጣጠሩ እንደምትችሉ አውቃለሁ፤ነገር ግን ከእናንተ ሲለዩ በራሳቸው መንገድ የሚሄዱ ይሆናሉ። ታማኝ እና እውነተኛ ሆነው እንዲቀጥሉ የሚያደርጋቸው ብቸኛ ምክንያት ፍቅር ነው። እግዚአብሔር እና ኢየሱስ በፍርሀት ላይ ሳይሆን በፍቅር ላይ ለመገንባት ጥበበኞች ነበሩ። ስለዚህ፤ የእግዚአብሔርን ቃል መጠበቅ ማለት ደቀመዝሙር ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር

የሚፈተንበት ትልቁ ፈተና ነው፡ “ማንም እኔን የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል።” እናም ፍቅር ለመታዘዝ ምክንያት ነው።

ከዛም እርሱ “ማንም እኔን የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤አባቴም ይወደዋል” ይላል።—ያ ሌላ ድንቅ እውነት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል መጠበቅ እግዚአብሔር አብ ልዩ በሆነ ፍቅር እንዲወደን ያደርገናል። አሁን፤እግዚአብሔር ዓለምን በሙሉ በሆነ መንገድ ይወዳል፤ነገር ግን እግዚአብሔር እውነተኛ ቃሉን ለሚጠብቁ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት የተለየ አይነት ፍቅር አለው።

ከዚያም፤ይሁዳ የጠየቀው አይነት "ጌታ ሆይ÷ ለዓለም ሳይሆን ራስህን ለእኛ ልትገልጥ ያለህ እንዴት ነው?” የሚል ጥያቄ ነበረን። የኢየሱስም መልስ "ማንም የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል" የሚል ነበር።ስለዚህ ክርስቶስ ራሱን እንዴት ለእኛ ይገልጣል? ኢየሱስ እራሱን የሚገልጠው በቃሉ ነው። ኢየሱስን በይበልጥ የምናውቀው የእግዚአብሔር ቃል በመጠበቅ ነው። ምናልባት ድንቅ መንፈሳዊ ልምምድ ሊኖረን ይችል ይሆናል፤ወደ ሦስተኛው ሰማይ ልንወሰድ እንችላለን ወይም ሌላም ሌላም። ግን ይህ ለአብዛኞቹ ሰዎች የሚሆን አይደለም፤እንዲሁም እግዚአብሔር ሆነ ኢየሱስ ራሱን የሚገልጥበት መሰረታዊ መንገድም አይደለም። መስረታዊው መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል በመጠበቅ ነው።

በመጨረሻም፤ይህን አስደናቂ ዓረፍተ ነገር እንመለክት “ማንም ቢወደኝ፤አባቴ ይወደዋል፤እኛ ወደ እርሱ እንመጣለን፤ቤታችንን እናደርጋለን” በማለት ይናገራል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር የብዙ ቁጥር ተውላጠ ስም የሚጠቀስበት ስፍራ በጣም ትንሽ ነው፤ነገር ግን ይህ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ነው። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል እኔ አባቴ እንዲሁም እኔ እና አባቴ ወደ እርሱ እንመጣለን፤መኖሪያም እናዘጋጃለን። ያ እጅግ ትንፋሽ የሚሰርቅ አስደናቂ የሆነ መግለጫ ነው፤እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር ወልድ መጥተው ከእኛ ጋር ሊሆኑ ይፈልጋሉ።ዳሩ ግን ያ እንዴት ነው የሚሆነው? በቃሉ ነው። የቃሉ አፍቃሪዎች ካልሆንን፤ለቃሉ የማንታዘዝ ከሆንን፤እግዚአብሔር የእርሱን ማደሪያ ከእኛ ጋር አያደርገውም።

እናም ዛሬ ጠዋት ስጨርስ እንዲህ ማለት እችላለሁ፤እጅግ አስገራሚ ሀሳብ ነው።ቃሉን ከመውደድ በበለጠ እግዚአብሔርን አትወዱም። ስለዚህ ምን ያህል እግዚአብሔርን በእውነት እንደሚወዱ ማወቅ ከፈለጉ፤ እግዚአብሔር በህይወትዎ ውስጥ ምን ያህል ቦታ እንዳለው ማወቅ ከፈለጉ፤ማወቅ ይችላሉ።ስለዚህ ነገር የምትገምቱት ሳይሆን፤ራሳችሁን “መጽሐፍ ቅዱስን ምን ያህል እወደዋለሁ? መጽሐፍ ቅዱስ በሕይወቴ ውስጥ ምን ያህል ቦታ አለው?” ብቻ በማለት እራሳችሁን ትጠይቃላችሁ፤ምክንያቱም ይሄ እኔ እግዚአብሔርን የምወደው ያህል ነው፤ይህ

በሕይወቱ ለእግዚአብሔር የሰጠውትን ቦታ ያህል ነው።

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገሩትን እነዚያን አምስት ዓረፍተ ነገሮች ጠቅለል አድርጌ ላስቀምጣቸው ምክንያቱም ወሳኝ ናቸውና። ተመልከቱ፤ብዙ ክርስቲያኖች በጨለማ ክልል ውስጥ ነው ያሉት፤እነርሱ የትኛው ብርሃን እና የትኛው ጨለማ እንደሆነ በትክክል አያውቁም። ይመኛሉ እንዲሁም ተስፋ ያደርጋሉ፤ነገር ግን እርግጠኛ አይደሉም። ምክንያቱ ደግሞ በህይወታቸው ለእግዚአብሔር ቃል ትክክለኛውን ስፍራ የሰጡ ስላልሆነ ነው።ስለዚህ እነዚህን አምስት ዓረፍተ ነገሮች ላስቀምጥና ከዚያ ላጠቃልል።

በመጀመሪያ ደረጃ፤የእግዚአብሔርን ቃል መጠበቅ እውነተኛ ደቀ መዛሙርትን ከዓለም ይለያል።

በሁለተኛ ደረጃ፤የእግዚአብሔርን ቃል መጠበቅ ማለት ደቀመዝሙር ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር የሚፈተንበት ትልቁ ፈተና ነው።ፍቅር ለመታዘዝ ምክንያት፤እንጂ ፍርኃት አይደለም።

ሦስተኛ፤የእግዚአብሔርን ቃል መጠበቅ ደቀመዛሙር የእግዚአብሔር ፍቅር ይኖረው ዘንድ ትልቅ ምክንያት ነው። እግዚአብሔር ደቀመዛሙርትን በልዩ መንገድ ይወዳቸዋል። እርሱ ዓለምን ሁሉ ይወዳል፤ነገር ግን ለደቀመዛሙርቱ ልዩ ፍቅር አለው። ዳሩ ግን፤እንደ ደቀመዛሙርቱ የሚወዳቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የሚጠብቁ ናቸው።በተለይ ለእግዚአብሔር ልዩ ወዳጅ መሆን ከፈለጋችሁ ቃሉን መጠበቅ አለባችሁ።

አራተኛ፤የእግዚአብሔር ቃል በመጠበቅ እና በመታዘዝ፤ክርስቶስ ራሱን ለእኛ ይገልጻል። ጥያቄውም "ራስህን ለዓለም ሳይሆን ለእኛ እንዴት ትገልጣለህ?" የሚል ነበር።ኢየሱስ እንዲህ አለ፤"እኔን የምትወዱኝ ከሆነ ቃሌን ትጠብቃላችሁ። እኔ ራሴ ማንነቴን የማሳየው በዚያ መንገድ ነውና።"

በመጨረሻም፤በእግዚአብሔር ቃል በኩል አብ እና ወልድ በአንድነት መጥተው ከእኛ ዘንድ ይኖራሉ።ይህ አስገራሚ ሐሳብ አይደለምን? ትንፋሼን ይወስደዋል። እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር ወልድ ከእኛ ጋር መኖርን ይፈልጋሉ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን ቃል በምንጠብቅበት ጊዜ ብቻ ይሰራሉ።

ሁላችንም በአንድነት በመጸለይ ልዘጋው።

"የሰማይ አባት፤ስለ ቃልህ፤ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነው መጽሐፍ ቅዱስ እናመሰግንሃለን። ይህ ለኛ መብራት እና ለመንገዳችንም ብርሃን፤የሚሰራ፤እውነተኛ እና የማይሻር ቃል ነው። እናም እጸልያለሁ፤ጌታ ሆይ፤እዚህ ለተሰበሰበው እና በመጨረሻም ከዚህ መልዕክት ጋር ለተገናኙ ሁሉ የቃልህ ወዳጆች እንሆን ዘንድ

ምክንያት እንዲሆነን ልጸልይ እፈልጋለሁ። ጸጋህ ቃልህን፤መጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት እንሆን ዘንድ በህወታችን ትክክለኛውን ስፍራ እንድንሰጥ ያስችለናል”